# ሃሽታጎች

ሃሽታጎች የማኅበራዊ ንቅናቄዎችን በማስተዋወቅ ረገድ ምን ያህል ውጤታማ እንደነበሩ እንማራለን። በተጨማሪም ተሳታፊዎች ሃሽታጎች በአንድ ንቅናቄ ዙሪያ ንቃት ለመፍጠር እንዴት እንድሚያግዙ ያውቃሉ፣ እንዲሁም የራሳቸውን ሃሽታግ የመፍጠር እና የሚፈልጉትን ዓላማ የማስተዋወቅ ዘዴ ይፈጥራሉ።

# አራማጅነት ሃሽታጎችን በመጠቀም

## ክፍል አንድ

### *ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው*

ምንም እንኳን ሰዎች ብዙውን ጊዜ በንቃት መፍጠር ዘመቻዎች ውስጥ ለአንድ ዓላማ አንድን የማኅበራዊ ሚዲያ ቢጠቀሙም፣ እነዚህ መድረኮች የሚያመሳስሏቸው አንዳንድ ባህሪዎች አሏቸው። አንዱ ጠቃሚ የጋራ ባህሪ ሃሽታግ ነው። ሃሽታጎች የእኛን ልጥፎች በተመሳሳይ ርዕስ ስር ካሉ ሌሎች ልጥፎች ጋር በማገናኘት ትኩረት እንዲያገኙ ያግዙናል። ለምሳሌ፣ በቅርብ ጊዜ ካካሄድነው አጥቂያችን ሃት ትሪክ የሰራበት የእግር ኳስ ጨዋታ የወሰድናቸውን ቪዲዮዎች ለማጋራት ብንፈልግ፣ “#football” እና “#hattrick” የሚሉትን ሃሽታጎች በቪዲዮው ማብራሪያ ውስጥ ማካተት እና ስለ የእግር ኳስ ቪዲዮዎችን መመልከት ለሚፈልጉ ሰዎች እንዲያዩት ማስቻል እንችላለን። በዚህ መንገድ ፕሮፌሽናል የእግርኳስ ችሎታ ፈላጊዎች የእኛን ቪዲዮዎች እንዲመለከቱ የሚኖረውን ዕድል እንጨምረዋለን።

ሃሽታጎች በተለይ ለንቃት መፍጠር ፕሮጀክቶች ጠቃሚ ናቸው። ለምሳሌ፣ በፍሎሪዳ ዩኤስኤ ከትራይቮን ማርቲን በፖሊስ ጥይት መመታት በኋላ፣ በርካታ ተሟጓቾች በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ስላለው የዘር ግንኙነት #BlackLivesMatter የሚለውን ሃሽታግ በማካተት ልጥፎችን መጻፍ ጀምረው ነበር። ሃሽታጉ ከቀን ወደቀን በብዙ ሰዎች እየታወቀ ሲመጣ፣ በየጊዜው ተጨማሪ ሰዎች ጠይም ግሰቦች ከፖሊሶች ጋር ስለገጠሟቸው የግል ገጠመኞች እና በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከፖሊስ ጋር ያጋጥጠማቸውን እሰጥ አገባ #blackLivesMatter የሚለውን ሃሽታግ በመፈለግ ማግኘትና ማየት ቻሉ። በማኅበራዊ ሚዲያ ንቅናቄ፣ Black Lives Matter በታላላቅ ሰዎች በመታገዝ ሰዎች ወደ ጠንካራ የተሟጋቾች ንቅናቄነት አደገ።

ሃሽታግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ጉልበት ያለው የማኅበራዊ ሚዲያ ቅርጽ ነው። ቦኮ ሃራም 276 ልጃገረዶችን ከናይጄሪያ ቺቦክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፍኖ በወሰደ ጊዜ፣ ናይጄሪያውያን በመስመር ላይ #BringBackOurGirls የተሰኘ ሃሽታግ በመጠቀም በማኅበራዊ ሚድያ ውስጥ በጉዳዩ ላይ ንቃት ለመፍጠር ሞክረዋል። ታዋቂ ግለሰቦች እና የማኅበረሰብ መሪዎች ዓላማውን በመደገፋቸው በፍጥነት አለማቀፋዊ ድጋፍ አግኝቷል።

በዓለም ዙሪያ ንቃት ለመፍጠር ሃሽታግ መጠቀምን በተመለከተ ሌሎች በርካታ ምሳሌዎች አሉ። ለምሳሌ፣ የሚክሲኮ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በ2012 የፕሬዚደንት ምርጫ ወቅት “#YoSoy132” ሃሽታግን ተጠቅመዋል፣ የሆንግ ኮንግ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በ2014 የዲሞክራሲ ተቃውሞዎች ወቅት በ“#umbrellarevolution” ዙሪያ ድጋፍ አሰባስበው ነበር፤ እንዲሁም የቺሊ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የትምህርት ስርዓቱ እንዲሻሻል ግፊት ለማሳደር “ #MovimientoEstudiantil” የተሰኘ ሃሽታግ ተጠቅመው ነበር።

ለአንድ ዓላማ በሚሟገቱ ጊዜ፣ ሃሳብዎን ለታዳሚዎች ለማድረስ ሃሽታጎችን መጠቀም ጠቃሚ መንገድ ነው። በሚቀጥለው መልመጃ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ውስጥ የሃሽታግን ጥቅሞች እንመረምራለን።

# ምድብ ሥራ

## ክፍል አንድ

**የክላስ መስተጋብር**

ተሳታፊዎችን በጥንድ ያደራጁ።

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

በባለ ሁለት አባላት ቡድን፣ በቅርቡ አንድን አላማ ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የዋለ አንድ ሃሽታግ አግኙ።

አንድ ጊዜ አንድ ሃሽታግ ካገኙ፣ የሚካሄዱ ውይይቶችን ይገምግሙ፣ በቡድንዎ ውስጥ ደግሞ በውይይት ላይ ያለው ምን እንደሆነ አጭር መግለጫ ያምጡ። ይህን አጭር መግለጫ በቃል ለተቀረው ቡድን ያቅርቡ።

ሃሽታግ ለማግኘት እና አጭር መግለጫውን ለማምጣት 15 ደቂቃ ይኖርዎታል።

**የክላስ መስተጋብር**

ተሳታፊዎች እንዲሰሩ 15 ደቂቃ ይስጧቸው። ከጨረሱ በኋላ፣ ለእያንዳንዱ ጥንድ አጭር መግለጫቸውን ለቡድኑ እንዲያቀርቡ ለእያንዳንዳቸው 15 ደቂቃ ይስጡ።

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

ሃሽታጎችን በመጠቀም እየተጋራ ያለው ምን አይነት ይዘት ነው?

በእነዚህ ሃሽታጎች ስር እየተካሄዱ ያሉ ተመሳሳይ ውይይቶች አሉ? ይህ እየተከናወነ ያልሆነው ለምንድነው ብለው ያስባሉ?

አንዳንድ ሃሽታጎች ከሌሎቹ የበለጠ ውጤታማ (ለምሳሌ በድጋሚ ለመለጠፍ የበለጠ ዕድል ያላቸው) የሆኑ ይመስላሉ? የትኞቹ ናቸው? ለምን?

## ክፍል ሁለት

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

አሁን ለእርስዎ ጥንድ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ያምጡ፡-

1. ሃሽታግ ይፍጠሩለት።

2. ሃሽታግዎን ለማስተዋወቅ አንድ ምስል፣ ኢንፎግራፊክ፣ ሜም፣ ገበታ፣ ወይም ግራፍ ይንደፉለት።

3. ከአጋርዎ ጋር፣ ሃሽታግዎን በአንድ መረብ ውስጥ ለማዛመት የተለያዩ መንገዶች ላይ ይወያዩ። ሌሎች ሃሽታጎችን ከመመርመር የተማርናቸው አንዳንድ ስኬታማ ስትራቴጂዎች ምንድናቸው?

ይህን ልምምድ ለማጠናቀቅ 30 ደቂቃዎች አሏችሁ።

**የክላስ መስተጋብር**

ይህን ልምምድ ለማጠናቀቅ ለተሳታፊዎች ከአጋራቸው ጋር 30 ደቂቃ ይስጧቸው። ከዚያ በኋላ፣ ጥንዶቹ ከትልቁ ቡድን ጋር ስለ ሃሽታጋቸው፣ ተያያዥ ስዕላዊ መግለጫዎች፣ እና ሃሽታጉን ለማዛመት የታሰቡ ሃሳቦች እንዲወያዩ 20 ደቂቃ ይስጧቸው።

ይህ መማሪያ ነገር በ Berkman Klein Center for Internet &amp ላይ በወጣት እና ሚድያ የቀረበ ነው; ሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ሶሳይቲ በ Creative Commons Attribution-ShareAlike 4.0 International ፈቃድ ስር። ወጣት እና ሚድያን እንደ ኦርጂናል ምንጭ እስከጠቀሱ እና ተጨማሪ ስራዎችን በተመሳሳይ ስምምነት መሰረት እስካከናወኑ ድረስ ከሱ የተወሰዱ ንግዳዊም ንግዳዊ ያልሆኑም ከሱ የተወሰዱ ነገሮች መጠቀም ይችላሉ። እነዚህን እና ተጨማሪ መማሪያ ነገሮችም Berkman Klein's Digital Literacy Resource Platform መስመር ላይ ይገኛሉ።